

# በተራራማዋ ቀለበትማ ሀገር ስለ ፀጋዬ ድህረ ገፅ ገለፃ ተደረገ።

*ሥርጉተ ሥላሴ*
*ሚያዝያ 2001 ዓ.ም.*

በስዊዘርላንድ በሉዘርን ከተማ የፀጋዬ ድምፅ ራዲዮ እና የፀጋዬ ድህረ ገፅ ዓላማ እና ተግባርን በሚመለከት ማብራሪያ ተሰጠ።

ስዊዘርላንድ የአውሮፓ ክፍለ አካል ነው። ስዊዘርላንድ እጅግ ማረኪ እና ሰላም የሰፈነበት ሀገር ነው። የስዊዘርላንድ ዜጎችም ሰላማዊ እና ሰውን የማይነኩ ጠንቃቃ ናቸው። ስዊዞች ከወደዱ በማተባቸው የፀኑ፣ ተግባቢዎች እና ሰላምተኞችም ናቸው።

ስዊዞች ሥራ ወዳድ በመሆናቸው ሥራ ወዳድ ለሆኑት ኢትዮጵያውያንም ቢሆን ምቹ ናቸው። አበዛኞቹ የስዊዝ ዜጎች ሥነ - ምግባራቸው ሙሉዑ በመሆኑ ለእኛ ያላቸውም አክበሮት ሙሉዑ ነው። በረካታ ስዊዞች ኢትዮጵያውያንን በማደጎ ያሳድጋሉ፣ ይጋባሉም በንፁህ ጓደኝነትም ተቀራርበው ተሳስበው ይኖራሉ። ይህ ጤናማ ዕይታ ነው ለእኔ።

በሀገረ ስዊዘርላንድ ቀደም ባለው ጊዜ በመኖሪያ ፈቃድ በርካታ ችግር የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን በአንፃራዊነት ቆየት ላሉት የተሻለ ሁኔታ ይታያል። ካለፉት ዓመታት ጋራ ሲነፃፀር። እርግጥ ነው የሀገሪቱ ህጎች ጠበቅ እና ከረር ያሉ ናቸው። ለምሳሌ የጋበቻ ሆነ ትምህርት ለመቀጠል ወዘተ ...

አሁን እንደ ኢ.አ መስከረም 26 ያወጡት ስደተኛን የሚመለከተው ህግ በጣም ጠበቅ ያለ ነው። የሆነ ሆኖ ግን ስዊዝ ውስጥ ለአንድ ቀንም ቢሆን ካለ የጤና ኢንሹራንስ፣ ካለ የዕለት መጠለያ፣ እና ካለ ምግብ እንዲኖር የሚገመደልበት ስደተኛ የለም።

አሁን ወደተነሳሁበት በብላቴ ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን የተሰየመው ድህረ ገፅ ይፋ ተግባር በጀመረ በ15ኛው ቀን ስዊዝ ውስጥ በአንድ ዓለም ዓቀፍ ነፃ የመፃህፍት ድርጅት ድህረ ገፁ ዕውቅና አገኘ። ነፃ የመፃህፍት ድርጅቱ ዕውቅና መስጠቱ ብቻ ሳይሆን ለ40 የተለያዩ ድርጅቶች ... ማለትም መንግስታዊ ለሆኑ እና ላልሆኑ፣ እንዲሁም ለሰባአዊ ድርጅቶች፣ ለባህላዊ እና ወዳጅነት ቤተ-መፃህፍት ደበዳቤ በመፃፍ ሰፊ የማስተዋወቅ ተግባራትን ፈፀመልን።

... 2

በመጋቢት ወር መጨረሻ ላይ ደግሞ በስዊዝ የቱሪስቶች መናህሪያ እና የጲላቶስ ተራራ በሚገኝበት በሉዘርን ከተማ በሮሜሮ ህንፃ የኮሎንብያዊው የሃይማኖት መሪ የሮሜሮ 29ኛ የሙት ዓመት መታሰብያን ምክንያት በማድረግ በተካሄደው ሚዲያና ተገባሩን አወንታዊ እና አሉታዊ ገፅታውን በስፋት በገመገመው ሙያ ጠገብ በሆኑት የቴሌቢዥን፣ የሬዲዮ፣ የፕሬስ ሀገር አቀፍ ዕወቅ ባለሙያዎች ወርክ ሾፕ ላይ ዙሪክ በሚገኘው የሎራ ራድዮ የአካባቢ የፀጋየ ራድዮ፣ እና የፀጋዬ ድህረ ገፅ ዓላማ፣ ተግባር፣ ተልእኮ እና ክንውን በሚመለከት በተያዘልን ፕሮግራም መሰረት ማብራሪያ ተሰጥቷል። ተሳታፊዎችም የተሰጠውን ማብራሪያ በፅሞና በሙሉ አትኩሮት ተከታትለዋል። ግልፅ ባልሆኑት ጉዳዮችን በመጠዬቅ ገንቢ ውይይቶችን መካሄድ ተችሎዋል።



በዕለቱ ተሳታፊዎች የተመሰጡበት መሰረታዊ ጉዳይ በፋሽስቱ የኢትዮጵያ አስተዳደር የፕሬስ ነፃነት መዳፈን እና በክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ የግፍ እስር ላይ እየተፈፀመባት ያለው በደል እና ኢሰባዊ ድርጊት ላይ ነበር።

እንዲሁም በኢትዮጵያውያን ላይ ያለው የአፈና እና የጭቆና ሥርዓት ለማስወገድ በሚደረገው የሚዲያ ተግባር በሚመለከትም ሀገር ሊደርሱ በሚችሉ ራዲዮኖች ተገትን መስራት እንዳለብንም አሳስበዋል። ከእኔ በተጨማሪም በአጋዥነት የተመደቡልኝ ወ/ት ብላነካ ሽታይማን የወርክሾፑ የዝግጅት አሰተባባሪም በሀገራችን ላይ ስላለው ጠናና አስተዳደር የበኩላቸውን ጠንከራ አሰተያየት በመስጠት የተሳተፊዎችን ሙሉ አትኩሮት መሳብ ተችሏል።

ገለጣው በስላይድ የተደገፈ ሲሆን ብላቴ ጌታ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን በህይወት በነበረበት ወቅት በድምፁ ያቀረበው የእንግሊዘኛ ግጥም ቀርቧል፣ በሌላ በኩልም የብላቴ ጌታ ሎሬት ፀጋየ ገ/መድህን የህይወት ታሪክ በእንግሊዘኛ እና በጀርመንኛ ለተሳታፊዎች ታድሏል። በአጠቃላይ ሲታይ አጋጣሚው ጥሩ ተሳትፎም መልካም ነበር። ከዜህም ሌላ ሰለ ግንቦት 7 የፍራንከፈረት ስበሰባ እና ሰለለንደኑ ቀጣይ አወሮፓ አቀፍ ህዝባዊ ሰላማዊ ሰለፍም ጠቋሚ መረጃ ተሰጥቷል።

በማዕልቱ መግለጫ የሰጡት የተወዳጁ የብሊክ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ አቶ ቬርነር ዲ ሸፐር ሚዲያና ትረፉ፣ ፎቶግራፎች በፕሬስ ውጤቶች ላይ ስላላቸው ጉልህ ሚና፣ የጦርነትን አሰከፊ ገፅታ ላይ በማተኮር አሮጌው እና አዲሱ ሚዲያን ተግባር በንፅፅር ያቀረቡት ደግሞ  ወ/ሮ ዩዲት አሞልድ ሲሆኑ  የአማራጭ ሚዲያ ራዕይን በዝርዝር ያቀረቡት ዕውቁ ጋዜጠኛ እና የኮሚክ አርት ፀጋው ያላቸው አቶ ወልፍ ሉድቢግ፣ ነበሩ ...

አቶ ወልፍ በአምስት ነጥቦች ላይ በሁለት ምዕራፍ በመከፋፈል ሰፊ አትኩሮት አድርገዋል። መንፈሱ ... የሚዲያ ቤተሰብ በኤሽያ እና በአፍሪካ/ ኢትዮጵያ/፣ አዲሱ ሚዲያ የሀይል አስተዳደርን ወይንም አስገዳጅነትን ሰለመታገል፣ አየር ላይ ሰለሚውሉ ሚዲያ ጥራት በሚመለከትም ሂስ፣ ሚዲያ እና ዓለማችን፣ በመጨረሻም ስዊዝ ውስጥ በአካባቢ ራዲዮኖች ተሳተፎ/ኢትዮጵያን/ ለናሙና በመውሰድ በስፊት ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ወርክ ሾፑ በዋና ርዕሰ ጎዳዮች ላይ በጋራ ማብራሪያ ይሰጥ እና ውይይቱ የሚካሄደው ደግሞ በተለያዩ ክፍሎች ነበር፡፤

ወርክሾፑን ያዘጋጁት ድርጅቶች ..

1. LOGO(Amnesty International immensee)
2. LOGO(Arbeitsgrupe Schweiz/Swiss/-Kolumbien)
3. LOGO INTERTEAM(Fachleute im Entwicklungseinsatz)
4. LOGO(Theologische Bewegung für Solidarität und Befreiung
5. LOGO(Reformierte Kirche Kanton Luzern
6. LOGO (Fastenopfer) እነዚህ ነበሩ

ወርክሾፑ በተያዘለት ፕሮግራም መሰረት እ.አ. ሰዓት አቆጣጠር ከጥዋቱ 09.00 ተጀምሮ በጋራ ፀሎት እና በህብረት መዝሙር በሻማ መብራት ውሰጥ ትንሽ የጉዞ ራዲዮን ከተዘጋጀው ልዩ ቦታ ላይ በማስቀመጥ በአራት የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች በቅቅብል ዝግጅት እጅግ ልብን በሚመሰጥ ሁኔታ ልክ 17.00 ላይ ተፈፅሟል። አንድ ቁም ነገር ተማርኩኝ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ፈቃድ መጠዬቅ። እግዚአብሔርን ማስቀደም ... ለሀገረ ኢትዮጵያም ትንሳኤ መንገዱን ብንከተለው እናተርፍበታለን። እሱን የያዘ ምን የሚገደው ነገር አለ እና ... ሁሉ በርሱ ይሆናል።

*ቅዱስ እግዚአብሔር ሀገረ ኢትዮጵያን ይታደግ!!*
*አሜን!!*